አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
አስተዳደር ቦርድ ጽ/ቤት

Addis Ababa University
Board Office

251-11-123 97 52
251-11-123 97 74
E-mail: poffice@aau.edu.et

✉ 1176
Website: www.aau.edu.et

አዲስ አበባ
Addis Ababa

ኢትዮጵያ
Ethiopia

ቀን፡- ነሐሴ 9 ቀን 2011 ዓ.ም

ቁጥር፡- አአዩ/አ/ቦ/001/11/19

ከ፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ለ፡ የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ በሙሉ

**ጉዳዩ፡- ስለ አ.አ.ዩ. ሪቫይታላይዜሽን ጥናት ኮሚቴ መቋቋም**

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአገሪቱ አንጋፋ ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ መጠን ለአገሪቱ የተማረ የሰው ኃይል በማፍራት፣ ምርምርን በማጎልበትና ዕውቀትን በማስፋት ከግማሽ ምዕት ዓመት በላይ የተጫወተውን ቁልፍ ሚና ሁላችንም የምናውቀው ነው። ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተከሰቱ የውስጥና የውጭ ችግሮች ምክንያት ይህ የፊር ቀዳጅነቱ ሚና እየደበዘዘ መጥቷል። እነዚህ ችግሮች በወቅቱ ካልተፈቱ የዩኒቨርሲቲው ህልውና ራሱ አደጋ ላይ የሚወድቅበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል።

በአዲስ መልክ ተዋቅሮ የተቋቋመው የዩኒቨርሲተው አስተዳደር ቦርድ ዩኒቨርሲቲው ያለበትን ሁኔታ በጥልቅ መርምሮ ተቋሙ ከችግሩ ወጥቶ ዓለም አቀፋዊ ደረጃን እንዲጠብቅና ሀገራችንንና ኅብረተሰባችንን በከፍተኛ ደረጃ ሊያገለግል እንዲችል መደረግ እንዳለበት በፅኑ አምኗል። ስለሆነም አሁን የደረሰበትን ሁኔታ የሚገመግምና ወደተሻለ አቅጣጫም ለማሸጋገር የሚያስችሉ ምክረ ሐሳቦችን የሚያቀርብ ኮሚቴ አቋቁሟል።

ኮሚቴው ከዩኒቨርሲቲው አካደሚክ ማኅበረሰብ፣ ከቀድሞ የዩኒቨርሲቲ አባላት፣ ከግሉ ክፍለ ኤኮኖሚና በውጭ ከሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ምሁራን የተውጣጣ ሆኖ የተዋቀረ ሲሆን፤ አባላቱም ያለምንም ክፍያ እና ጥቅም በፈቃደኝነት ለማገልገል ቦርዱ ያቀረበላቸውን ጥሪ የተቀበሉ ናቸው። ኮሚቴው እስካሁን ባደረጋቸው ስብሰባዎችም ከቦርዱ በተሰጠው ኃላፊነትና መመሪያ መሠረት ተግባሩን በስኬት ለማከናወን የሚያስችለውን ፍኖተ ካርታ ነድፎ ሥራውን በማካሄድ ላይ ይገኛል። የዚህም ፍኖተ ካርታ አንድ ዋነኛ አካል የዩኒቨርሲቲውን ኅብረተሰብ የተለያዩ አካላት በጥልቅ በማወያየት ጠቃሚና አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ማሰባሰብ ነው፡

ይህ የኮሚቴው ተግባር ለዩኒቨርሲቲውና ከዚያም አልፎ ለሀገራችን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው እንደመሆኑ መጠን የሁሉም ያልተገደበና ያልተቆጠበ ትብብር ወሳኝ ነው። ስለሆነም የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ በሙሉ (ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ኃላፊዎች፣ የአስተደደር ሠራተኞች፣ ወዘተ) ኮሚቴው በሚያዘጋጀው መርሀ ግብር መሠረት ስኬታማ ሥራ እንዲሠራ ሙሉ ትብብራችሁን እንድትሰጡ እናሳስባለን። የጋራ ጉዳያችን በመሆኑም ይህ ትብብር እንደማይጓደል ሙሉ እምነት አለን።

ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ
የአ.አ.ዩ. አስተዳደር ቦርድ የትምህርት እና ምርምር ንዑስ ኮሚቴ አባል

ክብርት አምባሳደር ዶ/ር የሺመብራት መርሻ
የአ.አ.ዩ. አስተዳደር ቦርድ የትምህርት እና ምርምር ንዑስ ኮሚቴ አባል

Federal Democratic Republic Ethiopia
Addis Ababa University